# ሕዝብ የውርስ ሀብት አይደለም !!

አባት ወይም እናት ሲሞቱ የሚያወርሱት ንብረት ወይም ርስት ወይም የቤት ቆሳቁስ ፣ በጥቅሉ የውርስ ሀብት ይባላል ። በርግጥ ከረጅም ዘመናት ወይም ዓመታት በፊት በነበሩት ጥንታዊ የነገሥታት መስተዳድሮች አንድ ንጉሥ ወይም ንግሥት ስትሞት ወይም በአንድ አጋጣሚ ሥልጣን የመልቀቅ ነገር ሲመጣ ፣ ተተኪው አልጋ ወራሽ በዘር ንክኪው ብሎም በሀገሩ ሕገ-መንግሥት መሠረት እየተባለ ሀገሩንም ሕዝቡንም እንደ ውርስ ሀብት በመቁ ጠር የሥልጣነ መንግሥት ሽግግር ይፈጸማል ።

ሰዎች እያወቁ እየነቁና የግለሰብ ነፃነት መከበር ጥያቄ ከመጣ በኋላ ግን ፣ ሥልጣን በአ ንድ ዘውድ አገዛዝ ፣ ወይም በአንድ ግለሰብ ሥልጣነ-መንግሥት ወይም በአንድ ዘር ቀጣይ የውርስ አገዛዝ መቀጠል እንደሌለበት ታውቆ ፣ የተለያዩ ቀጣይ ግፈኛ አገዛዞች እየተሻሩ ፣ በምትካቸው ዲምክራሲያዊና ፥ ዲሞክራሲ-ለበስ መሰተዳድሮች እየተተኩ መምጣታቸውን ሳናስተውል አልቀረንም ። ሁለቱ መስተዳድሮች ማለትም ዲሞክራሲያዊና ፣ ዲሞክራሲ-ለበስ መስተዳድሮች ማንኛችንንም ግራ የሚያጋባ አይመስለኝም የሚል ግምት አለኝ ።

ዲሞክራሲያዊ መስተዳድር በዓለም አቀፍ ደረጃ ሙሉ ተልዕኮውን እንዳልመታና ፣ ገና እየተንቀረፈፈ ለመሆኑም ብዙዎች ይገነዘቡታልና አያከራክረንም ። ለዚሁም በአንድ መጽ ሐፍ ላይ ተጽፎ ያገኘሁትን ላስቀምጥ እወዳለሁ ፣ የመጽሐፉ መጠሪያ ፣- “ The story of amnesty international - “ ባጭሩ የሚለውን ልጥቀስ ፣- Democracy has been thr- oughout the century a slow uncertain, but in the end steady cumulative process and now it is a hard thing for any one to block at least for any length of time.“

ሲል ይገልጸዋል ። በአንዳንድ ሀገሮችም ያለውን መስተዳድር ስንመለከት በቀጣይ ዘውዳዊ አገዛዝ ላይ ዲሞክራሲያዊ መስተዳድር መኖሩን እናስተውላለን ። ሆኖም ዲሞክራሲው ምን ያህል ጥቅም ሰጠ አልሰጠ ብለን መገምገሙን ለዚያው ተጠቃሚው ሕዝብ መተዉ ይሻላል ነው እኔ የምለው ። ዲሞክራሲ ለበስ መስተዳድሮች በዓለም ላይ ዝንጉርጉር ሆነው ከመታየታቸው በላይ ፣ በዲሞክራሲ ስም ስንት ጉድ ተፈጸመ ? ዲሞክራሲን መስጠትና መንፈግ የሚችሉት ግለሰቦች ወይም ጨቋኝ ገዥዎች ከሆኑ የያንዳንዱ ዜጋ ዲሞክራሲያዊ መብቱ ሰብዓዊ ክብሩ የት ነው ያለው ? የዲሞክራሲው ጽንሰ ሃሳብስ በዝንጉርጉር መልኩ የተቀመጠ ነው ወይስ አንድ-ወጥ ? ዜጋው በዲሞክራሲው መጠቀም ካልቻለ ዲሞክራሲ ለበስ መስተዳድሮች እንዴት በዕውነተኛው ዲሞክራሲ ስም ይነገራሉ ? የዓለም አቀፍ ኃያ ላንስ ዶሞክራሲ ለበስ አፈናውን ዲሞክራሲ ነው ብለው ሲጠሩ ፣ ጨቋኙን ዲክታተር መሪ ዲሞክራት ነው ብለው ሲጠሩት አያፍሩምን ? በዚህስ የዓለም-አቀፉ ማኅበረ-ሰብ ትሪካቸ ውን ያልነቃባቸውና የማይታዘባቸው መስሏቸው ይሆን ? ለማንኛውም ያሳዝናል !!!

ስለ ዲሞክራሲ ጥቅምና ጉዳት ፣ ወይም ስለ ዲሞራሲው ጽንሰ-ሃሳብና ሂደቱ እንወያይ ብንል እንደ አስተሳሰባችን ልዩነትና አመለካከታችን ብዙ የምንለያይበት ወይም የምንቀራ ረብበት ወይም የሚያስማሙን ሁኔታዎች እንደሚኖሩ አያጠራጥርም ። ዛሬ የዓለማት ሕዝቦች ጥቂቶች የተላበሱትን ዲሞክራሲ እኛም ልንቋደስና ሰብዓዊ መብታችንንም ልናስ ከብር ይገባናል ብለው እየተነሱ ነው ። ይህ ጥያቄ በዲሞክራሲ ለበስ ማወናበድና ዲክ ታተሮችን ሥልጣነ መንግሥት ላይ በማስቀመጥ ፣ የሕዝብን መብት በመርገጥ ካሁን በኋላ ዓለማችንን የሰላም አልባ ዓለም ማድረግ እንደማይቻል እርግጠኛ ሆኜ ነው የምናገረው ። ኃያላን በዚህ አስጠሊ አካሄድ ጨቋኞችን ዲሞክራት ናቸው ብለው ቢጓዙ ፣ መፃኤውን ፈተና እነሱም ቢሆኑ የሚያልፉት አይመስለኝም ። ምክንያቱም ከኋላው ሌላ መዘዝ ስለ ሚኖረው ነው ። ይኸው አሁን እንዳየነው ሁሉ !! ወደፊት የሚታዩትን አደገኛ ችግሮች ከወዲሁ በማርገብና ፣ ዓለማችንን በሕግ የምትመራ ቢያደርጓት የበለጠ ጥቅም ይኖራል የሚል ግምት ነው ያለኝ ። እንደ ምሳሌ ዊኪሊክን ብንመለከት በርካታና ድንቅ ሥራዎ ችን አሳይቷል !! ዊኪሊክ የዓለም አቀፍ ጭቁን ሕዝቦች የመታፈናቸው ውጤት ነው ! ማለት እንችላለን ። ምክንያቱም በጥሩ ገጸ-ቁመና መድረክ ላይ ቆመው ስለ ዲሞክራሲና ፣ የዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ ግንኙነት ሲዋሹ የነበሩት መሪዎች ሁሉ ከጀርባቸው ምን ያህል ቁሻሻ ነገር እንደተከማቸና መዋሸታቸውንም በግልጽ ስላሳየን ነው ። ስለዚህ ካሁን በኋላ ያለው የመጋለጥ ጉዳይ ዕድሜ ለነሱ ቴክኖሎጂ በቀላሉ ያፍራሉ ቢባል በቂ ነው !!

በማንኛውም ኅብረተ-ሰብ ታሪክ የመንግሥት ለውጥ አለ ። ለውጥ ያመጣል ተብሎ የሚታሰበው አመጽ የሕዝቡን ስሜት ተላብሶ መልካም ለውጥ ያመጣል ፣ አያመጣም ፣ ወይም አቅጣጫውን ስቶ ያልተጠበቀ ለውጥ ይከሰታል ለማለት ፣ ይህን የሚወስነው አካ ሄዱ ነው ። በዓለማችን ላይ ከደረሰው የኢኮኖሚ ድቀት በላይ በሙስና በተዘፈቀ ጨቋኝ አስተዳደራቸው ሕዝቡን የፊጥኝ አሥረው የሚያሰቃዩት የሆዳም መሪዎችን ተግባራት ሕዝቡ ከመንገፍገፉ የተነሳ ዛሬ በዓረቡ ዓለም ገንፍሎ የመጣው የጨቋኝ ገዥዎችን ከሥ ልጣን የማስወገድና የዲሞክራሲው ጥያቄ ለመላው ዓለም እንደሚዳረስ ልብ ያለው ልብ ይለዋል ። የ3ኛ ዓለም ሀገራት ሕዝቦች ጭቆና በቃኝ ፣ ዲሞክራሲን መላበስ አለብኝ ሲል ፣ ኃያላንና ጨቋኝ ገዥዎች በማስመሰሉ ዲሞክራሲ ውስጥ ታፍነህ መቆየት አለብህ ብለው

ሊወስኑ አይችሉምና ፤ እነሆ  የነፃነቱ ችቦ እየተቀጣጠለ !  ዲክታተርና አምባገነን ገዥዎች ንም  እያቃጠለ ነው ::    ሕዝብ የውርስ ሀብት አለመሆኑን ያልተረዱ እንደ ግብጹ   መሪ ሙባረክ ዓይነቶቹ ልጃቸውን ለሥልጣን ሊያዘጋጁ ነበር ግን አልተሳካም ::   መለስ ዜናዊ ራሱ  በደም የተጨማለቀው አልበቃ ብሎት ከሕዝብ የነጠቀውን ሥልጣን ቢችል ለልጆቹ ለሚስቱና ለተጠናወተው የዘር ዕምነት አጃቢዎቹ ለማስረከብና ፤  ኢትዮጵያን ባዶ ለማድ ረግ  አልተዘጋጀም የሚል ይኖራል ብዬ አላምንም ::  እና እዚህም ላይ የምንረዳው ነገር ችግሩ የጨቋኝ ገዥዎችን ጭቆና ብቻ ሳይሆን የኃያላንንም ተጽዕኖ ነው !!

## <u>ታዲያ የለውጡ እንቅስቃሴና ሂደቱ እንዴት ነው ለኛ የሚደርስና ውጤት የሚያመጣው ?</u>

አሁን ወደ ሀገራችን መለስ እንበልና ፤  ቀደም  የተካሄዱትን የለውጥ  እንቅስቃሴዎችና ውጤታቸውን  አሁን ካለንበት ዓለም-አቀፍ  የፖለቲካ  እንቅስቃሴ ጋር በማስተያየት ምን ማድረግ እንዳለብን እናስተውል :: ይህንንም ስንል የአብዛኛው መንግሥታት ሀገረ ሕዝቦች ከከወኑት ቁምነገር ትምህርት በመውሰድና ፤  ከኛም ደካማ ጎን አኳያ ምን አስወግደን ምን ማምጣት እንዳለብን ከመገንዘብ ጋር ቢሆን ይመረጣል  ::    ትርፍና ኪሣራችንን ሳናውቅ ለለውጥ የምናደርገው ትግል ፍሬ አልባ ይሆናል ብለን ከወዲሁ ማሰቡ  ፤ ሰው የመሆናችን መለኪያው በመሆኑ ፤ እስቲ ያሳለፍነውን የለውጥ ሂደታችንን በመጠኑ እንዳስውና ለአዲሱ የትግል ውጤት ዝግጁ እንሁን  ::

በ1950 ዎቹ ውስጥ በተካሄደው የመንግሥቱ ነዋይና ፤ ከዚያም በመንግሥቱ ኃይለ ማር ያም የተከወኑትን የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ማገናዘብ ስንሞክር ምን ያህል ልዩነት እንዳላ ቸውም እንረዳለን ማለት ነው ::

በመንግሥቱ ነዋይ የለውጥ እንቅስቃሴ ወቅት ፤  መንግሥቱ ነዋይ ጭቁኑ ሠርቶአደር ፤ ጭቁኑ ገበሬ ፤  እንዲሁም ጭቁኑ ወታደር ባልተደራጀበት ወቅት ነው የመጣው ::  ወይም ለዚህ አመጽ መንግሥቱ ከተጨቋኙ ጋር የፈጠረው ኅብረት አልነበረም ::  አለ ቢባል እንኳ በቂ  ነው ተብሎ  የተመዘገበ አይደለም ::  ስለዚህ የለውጡ  ሂደት በስሜታዊነት የተመራ በጠመንጃ ብቻ ለውጤት እበቃለሁ ከሚል ስሜት በመነሳሳት በመሆኑ ፤  አመጹ ለውጤት አልበቃም ::   ቢያንስ የክብር ዘበኛው ጦር ሙሉ በሙሉ  የመንግሥቱ ደጋፊ በሆነ ነበር ፤ ያ ባለመሆኑ ግን ውጤቱ ያስከተለውን ቅጣት ጥቂት የአመጹ አካላት ብቻ ናቸው የተቀበ ሉት ::  የክብር ዘበኛው ጦር ጉዳዩን በግልጽ አውቆ ለለውጥ ሲል ያደረገው መፈንቅለ መን ግሥት ባለመሆኑም ፤ በርካታ የክዘ ወታደሮች " ከወገኖቻችን ጋር በማናውቀው ነገር ደም አንቃባም ! " ብለው የተሰጣቸውን ጠመንጃ በሲቪል ልብስ እየቀየሩ ከአመፃው ወጭ መሆ ናቸው ግልጽ ነው ::  ብዙዎች በፈቃደኝነት ጠመንጃቸውን ለጦር ሠራዊቱ አስረክበው ነገ ሮች እስኪጣሩ በምርኮኛነት ሲቆዩ ፤  የክዘን ወታደሮች ከያሉበት ይዘን እንድናቀርብ ከጓ ደኞቼ ጋር ታዘን አሰሣ ስናደርግ ፤  ከያሉበት ጠመንጃቸውን ይዘው በመቅረብ እጃቸውን ሲሰጡን ፤  ያንኑ ቃል እየደገሙ ነበር ::<u>" እኛ ከወገኖቻችን ጋር ደም አንቃባም !!</u>

የአመፃ መሪዎቹን ልቦና ባናውቅም ለተበደለው ሕዝብ ተቆጭተው ይሁን፤ ወይም ኃይለ ሥላሴ መወገድ  አለባቸው ብለው ፤ ወይም ለሥልጣን ብለው እንደሆነ በግልጽ የወጣ ነገር ባይኖርም ፤  መንግሥቱ ነዋይ ለተጨቆነው ሕዝብ ሲል ነው !  የሚል ወሬ ከአንዳንድ ግለ ሰቦች ሲሠነዘር ፤ አንዳንዶች ደግሞ ለሥልጣን ብሎ ነው !  ወይም ሌላ  ተልዕኮ እንዳለው እየገለጹ  ነበር ::

ያንጊዜ ከተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ይልቅ በዚያው የለውጥ አካባቢ  በኃይለ ሥላሴ ላይ ሊከሰት የነበረው ሌላ ለውጥ  እጅግ አደገኛ ነበር ::   ከነበረኝ ትዝታ ትንሽ ልጠቁም ፈልጌ ነው ::  የኢትዮጵያ የጦር ኃይል ጭቁኑ ወታደር ይከፈለው የነበረው ደመወዝ አነስ ተኛ በመሆኑ ችግሩን ችሎ  ሀገሩን የሚያገለግል ወታደር እንደነበረ አስታውሳለሁ :: በዚያ ወቅት እኔም 18 ብር ደመወዝ የማገኝ ነበርሁ ::  እና ምን ሆነ ?  የጦሩን አመጽ ሊቀሰቀስ የሚያስችል  አንድ ሁኔታ ተፈጠረ ፤ ይኸውም በመከላከያ ሚኒስትሩ በሌ/ጄኔራል መርዕድ መንገሻ  አማካይነት የሚሊታሪው ሹማምንት በደመወዝ ጭማሪ ላይ ባደረጉት ምክክር ለኦ ፊሰሮች  ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪ ፤  ለበታች ሹማምንቱና ወታደሩ አነስተኛ  የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎ  ውሳኔው በንጉሡ ጸድቆ ለጦሩ ሲነገር ድንገተኛ አመጽ በመቀስቀሱ ነው :: ወታደሩ ከዳር እስከ ዳር ተንጫጫ ፤ በመድፈኛ ጦር አባል በሆነ አንድ የአምሳ አለቃ አማ ካይነት ለተቃውሞ ሰልፍ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ተደረገ ፤  የስብሰባውም ቀን ተወሰነ ::

የኃይለ ሥላሴን መንግሥት በማዳናችን ለያንዳንዱ ወታደር ሃምሳ ብር ጉርሻ በመስጠታ ቸው  ንጉሱን ብናመሰግንም ፤  በደመወዝ ጭማሪው አድልኦ ምክንያት  ብሶት  የተሰማው

ጦር ያለ ርኅራኄ ቆርጦ በመነሳት ፣ ኦፊሰሮቹን እሥር ቤት አስገብቶ በቀጥታ ወደ ቤተ መንግሥት አቀና ። ጃንሆይ ከላይኛው ቤተመንግሥት ስለነበሩ ተጠርተው መጡ ። ልዑላኑንና ሚኒስትሮቹን ይዘው በመቅረብ እኛ ከመናገራችን በፊት ንግግሩን እሳቸው ናቸው የከፈቱት !! " ችግር ካለ ይኼን ያህል ሆናችሁ ከምትመጡ 15-20 ሆናችሁ ብትመጡ ውሳኔ ይሰጣችሁ አልነበረም ? አሁን ይኸን ያህል ሆናችሁ መምጣታችሁ ማንን ለማስፈራራት ነው ? ከሁሉ የሚያሳዝነው እነዚህን ወጣትና ታዳጊ ወታደሮች ተንኮል ማስተማራችሁ ነው !! " ብለው በዚያን ጊዜ ልጆች ወደነበርነው ጣታቸውን ወደኛ ጠቁመው የብስጭት መልክ አሳዩ ። ጦሩ በጃንሆይ አነጋገር አጉረመረመ ! " እንግሊዝና አሜሪካንን ተመክተው ! " ነው የሚል ጉምጉምታ ይሰማ ነበር ። ከዚያም የተቃውሞ ሰልፍ መሪው የጦሩን ብሶት እንዲያሰማ ተደርጎ ጽሁፉን አነበነበው ። ግን በጣም ትዝ የሚለኝ ፣ በርካታ ወታደሮች ለጥያቄ እጃቸውን አንስተው ስለነበረ ፣ በተለይ አንዱ ወታደር ሲናገር ጃንሆይንም አስቋቸው የነበረው በፍጹም አልተረሳኝም ። ምን አለ ወታደሩ ?

" ግርማዊ ሆይ እንደሚታወቀው ወታደሩና ሲቪሉ በጉርብትና አብሮ ነው የሚኖረው ! በባኅላዊ ልማዳችንም ጎረቤቱ ቡና ተጠራርቶ የተገኘውን በፍቅር ይቋደሳል ! ከሲቪሎቹ ቤት ስንሄድ አንዳንድ ጊዜ ለቡና ቁርስ ተብሎ የነጭ ጤፍ እንጀራ ይቀርባልና በጣም ደስ እያለኝ ነው የምበላው ! በኔ በወታደሩ ቤት ተጠርተው ሲመጡና ለቡናው መቃመሻ የምናቀርበውን እንጀራ ቀምሰው ! " አይ የኢትዮጵያ ወታደር ወገብህን በበሬ ቆዳ አስረህ አሽዋ ነው የምትበላው ? " ይሉናል !! ለምንድነው ይህን የመሰለ ችግር የሚደርስብን ? ደመወዛችን በቂ ባለመሆኑ ፣ ለቤት ኪራይና ለልጆቻችንም አንዳንድ ወጪ ስለማይሸፍን ልን አይደለምን ? " በሚል ተናግሮ ሲያበቃ ጃንሆይ የወታደሩ ነገር አሳቃቸው !! እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ጃንሆይ ሲስቁ ያየሁትና ተገረምሁ !! ወዲያው ደመወዝ እንደሚጨመር ቃል ይገባሉ ፣ ጦሩ ግን አሁን ውሳኔ ካልሰማን አይሆንም ብሎ በመጨከኑ ፣ ትዝ እንደሚለኝ ጄኔራል ጃገማ ኬሎና ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ የሚባሉ ተወክለው ስታዲዮም ከወሰዱን በኋላ ዛሬውኑ ማታ ደመወዝ ጭማሪው በሬዲዮ ይነገራል ብለውን ሰልፉ ተበተነ ። እንደተባለውም ጭማሪው በሬዲዮ ተነግሮ የምሥራቹን የሰማው ጭቁን ወታደርም ደስ ብሎት አመሸ ።

እዚህ ላይ የምናስተውለው ነገር ምንድነው ? በአንድ ድምጽ ተባብሮ መነሳት ምንያህል ጠቃሚ እንደሆነ ነው ። መንግሥቱ ኃይለማርያም በመጣበት ወቅት ፣ ሠርቶ አደሩ ገበሬውና ተማሪው ወታደሩ ባጠቃላይም ጭቁኑ ሕዝብ እስከ አፍንጫው የደረሰ የኑሮ ምሬት ላይ ስለነበረ ፣ ታክሲ ነጂው ሴትኛ አዳሪና በረንዳ አደሩ ሳይቀር አነሳሳቸው በአንድነት ስለነበረ ፣ ለውጥ ለማምጣት ብዙ አልተቸገሩም ። ደርግ የጭቁኑን ሕዝብ ሥልጣን ቢነጥቅም ፣ የተነሱበት ዓላማ ግን አልከሸፈም ። ሃተታ ውስጥ ብዙ ጠልቄ ሳልገባ ሃሳቤን ግን በቀላሉ እንደምትረዱልኝ ይሰማኛል ። ይኸውም ፣ -

1- የተከፋፈለ ሕዝብ ለለውጥ ቢነሳ ትርፉ ወድቆ መሳባበር እንጂ ፣ ያሰበው ተሳክቶለት ለውጤት አይበቃም ። የእስከ ዛሬው ፖለቲካችንም ሂደት ይኸው ነበር !!

2- ዘር ጎሣና ሃይማኖታዊ ባላንጣነትን አንግቦ ዲክታተር ገዥዎችን አስወግዶ ለዲሞክራሲያዊ ውጤትና ለድል መብቃት አይቻልም !-

3- ዘረኛነት በራሱ የዲሞክራሲ ጸር በመሆኑ ዓለም-አቀፋዊ የፖለቲካ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር ሳይሆን ፣ ታላቅ ጋሬጣ ነው ።

4- በአሁኑ ወቅት ዘር ጎሣና ሃይማኖታዊ ባላንጣነትን አንግበው የትግሉን መሪነት የጨበጡት ኃይላት በእርግጠኝነት ሕዝብን ወግነው እንዳልቆሙና በወርሃዊ ድርጎ የራሳቸውን ሕይወት በተደላደለ ዘዴ እያኖሩ ፣ ኅብረተሰቡን ለጨቋኝ ገዥዎች ጭዳ በማቅረብ ያንተ ዘር ነገ ከሁሉ በላይ ይሆናል እያሉ የተስፋ ዳቦ እንደሚያስገምጡት !! ይህንን ቀደም አድርገን እናውቀዋለን !! ። የኛ የፖለቲካ መሪዎች እርስበርስ እየተፋጁ ሕዝቡ ነፃነትን እንዳይጎናጸፍ አድርገውት እስከዛሬ የተጫወቱበትም ከዚያው ከራስ ወዳድነት ጎራ ውስጥ ተወሽቀው የግል ጥቅማቸውን ስላስከበሩ እንጂ ፣ በዕውነትና ሐቅ በተሞላው ርዕዮት ለሀገርና ለወገን ብለው ቆመው ቢሆን ትግሉ እስካሁን ባልተጓተተና የሕዝባችን መከራ ተቀባይነት ባልተራዘመ ነበር !!!

ይህ አሁን በዓለማችን እየነፈሰ ያለው የዲሞክራሲ የሰብዓዊ ፍጡር መብትና የኢኮኖሚ ድቀት ያስከተለው ጥያቄ ፣ በኢትዮጵያችን ዓየር ላይ ይነፍሳል ወይም አይነፍስም ለማለት ከላይ የተገለጹት ሁኔታዎች ትልቅ ግንዛቤ እንደሚሰጡን እርግጠኛ ነኝ ። አንተ የጳውሎስ ነህ ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ ! ማለት ጠቃሚ እንዳልሆነ በዚህ 21ኛው ክፍለ ዘመን ያለን ሰዎች በጥብቅ እንገነዘባለን ! እኛ ሰዎች ነን ፈጣሪውም ኃያሉ ጌታ እግዚአብሔር ነው !! ማለት ግን ማንንም አይጎዳም ። የፖለቲካ ልዩነታችንን በክብ ጠረጴዛ ለመፍታት ወስነን ! እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን በማለት ፣ የተነጠቅነውን ዲሞክራሲ ለማምጣት በአንድነት ብንቆም ጥቅም እንጂ ኪሣራ እንደሌለው የሁላችን ልቦና ያውቀዋል ። በአሁኑ ዓለም እያንዳንዱ

መንግሥት ኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ከመግባቱ የተነሳ ፤ የወደፊቱ የስደት ሕይወት ፈጽሞ ዋጋ እንደሌለው የማይረዳ ሕዝብ ይኖራል የሚል ግምት የለኝም ። ስለዚህ በራስህ የደለ በች ሀገር ውስጥ በአንድ ሕዝብነትህ ተከባብረህ ዲሞክራሲን ተላብሰህ ከመኖር ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ እንደሌለህ ከወዲሁ ወገኔን እመክራለሁ !!

በተለይ በወያኔ ሁለገብ ሜዲያ አቀፍ በሆኑ ውዥንብሮች ፤ ይልቁንም በፓልቶኩ ውስጥ በሚካሄድ ወያኔያዊ ደደብ የፖለቲካ ውይይት ሕዝባችን ለዲሞክራሲ ያለው ጥያቄ ዕውን እንዳይሆን በውዥንብር እየተሞላ ፤ የሀገር ቤቱን ሕዝብና ውጭ ያለውን ሕዝብ በትግሉ ጎራ አንድ ሆኖ የሠከነ ፖለቲካ እንዳያካሂድ ፤ እንዲያውም ግንኙነት እንዳይኖረው የሠለጠነውን ዓለም መገናኛ ብዙሃን ለራሳቸው ጥቅምና ፤ የጭቁኑን ሕዝብ ፖለቲካዊ ጥያቄ ማፈኛ አድርገው እነሆ ለሃያ ዓመታት ወያኔና ጌቶቹ እንዲቀልዱብን ተደርጓል ። በሁላች ንም ዘንድ እንደሚታወቀው እርስ በርስ እየተናቆርን ፤ ራዕይ ያላቸውንም መሪ አጥተን ፤ ለወደፊቱም እንደ ሲኅናዎች ሀገርና መንግሥት አልባነትን እየተጠባበቅን ያለን ስለመሰለኝ ይህንን ሕዝብ ምን ነካው ? እያልሁ በመሥጋት በየቀኑ እየተሸማቀቅሁ ነው !!

ስለዚህ የሀገር ቤቱ ሕዝብና የዲያስፖራው እየተባለ ፤ ትግሉን በጋራ እንዳይወጡ የሚ ካሄደው አፈና ፤ ለአንድነቱና ለብርቅዬዋ ኢትዮጵያ ጠንካራ ዕምነቱ ያለን ሁሉ ልንቋቋ መው ስለሚገባ ፤ የጋራ ትግላችንን በማጠናከር በዚህ የዓለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊ ትኩስ ዓየር ወያኔና አበሮቹ እንደበታቸው እንዲዘጋ ማድረግ አለብን ። አንዳንድ ወገኖች ያዋ ጣናል ብላችሁ ከወያኔ ጋር የጀመራችሁት ግንኙነት እንደማይጠቅማችሁና ፤ ለዳግማዊ ስደት የሚዳርጋችሁ በመሆኑ ፤ ሳይመሽ አቅጣጫችሁን ብትቀይሩና የወያኔን ውዥንብር ንቃችሁ ለሰላም ብትቆሙ ይመረጣል ። ከመሰልቸት የተነሳ ከፖለቲካው ራሳችሁን ያገለላችሁትም እንደገና በመሰባሰብ የሀገር ቤቱን ሕዝብ በመቀስቀስና በምትችሉት እየ ረዳችሁና ፤ ትግሉን በሀገር ውስጥና በውጭ አጠናክራችሁ ፤ ወያኔን መጣልና በወያኔም ውድቀት ላይ በቀጥታ መንግሥታዊ ሥልጣኑን መረከብ የሚችል ኃይል ከወዲሁ በማደራ ጀት ክፍቱን ቦታ / vacuum/ በመሙላት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ማዳን የሚጠበቅብን መሆኑን ላረጋግጥ እወዳለሁ ። ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነውና እንጠቀመበት !!!

የኢትዮጵያ ትንሣኤ ቅርብ ነው !!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!

<u>አቤ ኮስትሬ</u>